# የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

## የንብረት አስተዳደር መመሪያ
## ቁጥር 327/2013

ሚያዝያ 2008 ዓ/ም

# የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ
# የንብረት አስተዳደር መመሪያ

## መግቢያ

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ/203/2003 የተቋቋመ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ነው፡፡ ኤጀንሲው ከጡረታ ፈንድ በሚመደብ በጀት እንደሚተዳደር በዚሁ ደንብ አንቀጽ 11 ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት የተቋሙን የአስተዳደር ፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግና ግልጽ አሰራር በተከተለ ሁኔታ በስራ ላይ ማዋልና ስራውን ስርዓት ባለው መንገድ መምራት ያስፈልጋል፡፡ መስሪያ ቤቱ ከጡረታ ፈንዱ በሚመደብ ገቢ የሚተዳደር በመሆኑ የራሱ የሆነ የንብረት አስተዳደር ፖሊሲና መመሪያ ሊኖረው እንደሚገባ በውጪ ኦዲት፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባለሙያዎች አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ከዚሁ አንጻር በኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት፣ በሪጅን፣ በቅርንጫፍና በመስክ ጽ/ቤቶች ያለውን ቋሚ ንብረት በአግባቡ መመዝገብና ማስተዳደር እንዲሁም የንብረት አወጋገድን የሚመራበት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ማውጣት አስፈለጊ ሆኖ መገኘቱ ይህ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 327/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2 ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

2.1 "ዕቃ" ማለት በጠጣር፣በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሳሪያ፣ ሸቀጥ፣ ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍትዌር፣ ሲሆን ከሚገዛው ዕቃ ጋር ግንኙነት ያለውን እና ከዕቃዎቹ ዋጋ ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት፣ የጥገናና ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎትን ይጨምራል፡፡

2.2 "አገልግሎት" ማለት ከዕቃ፣ ከግንባታ ዘርፍ ስራ እና ከምክር አግለግሎት ውጪ ያለ ሲሆን፣ የጥገና፣ የጥበቃ፣ የጽዳት አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን እና የውሀ አቅርቦት የመሳሰሉትን ይጨምራል፡፡

2.3 "የግንባታ ዘርፉ ስራ" ማለት ከህንጻ፣ ከዋና መስሪያ ቤትና ጽ/ቤቶች ግንባታዎች ስራ ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ ደረጃ የማሳደግ፣ የማፍረስ፣ የጥገና፣ የማደስ ስራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ስራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን፣ የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ስራውን የማንቀሳቀስና የማስተላለፍ ውሎችን ይጨምራል፡፡

2.4 "የምክር አገልግሎት" ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣የዲዛይን እና ቁጥጥር፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንብኞች ምክር የመስጠት፣ ስልጠና የመስጠት እና ዕውቀትን የማስተላለፍ አማካሪነት ባህሪ ያለው የአዕምሮ አገልግሎት ነው፡፡

2.5 "ግዥ" ማለት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ስራዎችን እና አገልግሎቶችን በግዥ፣በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል ማግኘት ነው፡፡

2.6 "አቅራቢ" ማለት ለኤጀንሲው መስሪያ ቤት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ስራ ለማከናወን ውል የገባ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

2.7 "ዕጩ ተወዳዳሪ" ማለት በኤጀንሲው በወጣ ጨረታ ግዥ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም ለመካፈል ያመለከተ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

2.8 "ተጫራች" ማለት የመጫረቻ ሀሳብ ያቀረበ ሰው ነው፡፡

2.9 "የጨረታ ሰነድ" ማለት ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በኤጀንሲው መስሪያ ቤት የሚዘጋጅ ዝርዝር የግዥ ፍላጎትን የሚገልጽ ሰነድ ነው፡፡

2.10 "የመጫረቻ ሰነድ" ማለት የኤጀንሲው መስሪያ ቤት ለግዥው ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መነሻነት ተጫራች በግዥው ለመሳተፍ የሚያቀርበው ሰነድ ነው፡፡

2.11 "የጥበቃ ሀላፊነት" ማለት በኤጀንሲው መስሪያ ቤት የበላይ ሀላፊ ወይም ሀላፊው በወከለው የሥራ መሪ፣ የመንግስት ንብረት እስከሚወገድ ወይም ከመዝገብ እስከሚሰረዝ ወይም በሌላ ሰራተኛ ወይም መስሪያ ቤት ጥበቃ ስር እንዲውል እስከሚተላለፍ ድረስ ንብረት ለመያዝና ለመጠበቅ፣ ለኤጀንሲው ሰራተኞች የሚሰጥ ሀላፊነት ነው፡፡

2.12 "የሕይወት ዘመን ስርዓት" ማለት ከኤጀንሲው ንብረት ጋር የተያያዙ ተግባሮች እና ወጪዎችን የማቀድ፣የመያዝ፣የመረከብ፣ የመጠቀም፣ የጥገና፣የፍጆታ ወይም የማስወገድ ወይም ከመዝገብ የመሰረዝ ተግባራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የኤጀንሲው ንብረት አስተዳደር እና ቁጥጥር ብቃት ባለው መንገድ እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ነው፡፡

2.13 "ማስወገድ" ማለት የኤጀንሲውን ንብረት በሽያጭ ወይም በዝውውር ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ወይም መቅበር ወይም ማቃጠል ነው፡፡

2.14 "ተሽከርካሪ" ማለት በመንገድ ላይ በሞተር ሀይል የሚንቀሳቀስ ወይም የሚጐተት ለሰው እና/ወይም ለዕቃ ማጓጓዣ የሚውል ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ነው፣

2.15 "የእርጅና ቅናሽ" ማለት ንብረቱ ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ ይሰጣል ተብሎ በሚገመትበት ዕድሜ ስርዓት ባለው አኳኋን የንብረቱን ዋጋ እንደወጪ እያሰቡ መቀነስ ማለት ነው::

2.16 "ስቶክ" ማለት በመስሪያ ቤቱ የተመረቱ ወይም የተገዙ ወይም በእርዳታ የተገኙ ንብረቶች ሆነው በመደበኛው የስራ እንቅስቃሴ ውስጥ አገልግሎት ላይ እስከሚውሉ ድረስ በመጋዘን የተቀመጡ ቋሚ ዕቃዎች፣ መሳሪያዎችና አላቂ ዕቃዎች ማለት ነው:: ሆኖም አገልግሎት ላይ ውለው የሚመለሱ ዕቃዎችን አይመለከትም::

2.17 "ኤጀንሲ"ማለት የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ነው፡፡

2.18 "የኤጀንሲው ንብረት ክፍል" ማለት የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ዋና መ/ቤት፣ የሪጅን ጽ/ቤቶችና ቅ/ጽ/ቤቶች የዕቃ ማከማቻ/ማስቀመጫ ክፍሎች ናቸው::

2.19 "የበላይ ሀላፊ" ማለት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በመንግስት በውክልና የተመደበ ኃላፊ ነው፡፡

2.20 "የኤጀንሲው ፋይናንስ ክፍል" ማለት በኤጀንሲው ዋና መ/ቤት፣ በሪጅንና በቅጽ/ቤቶች ደረጃ የሂሳብ ስራ የሚያከናውንበት የስራ ክፍል ነው፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ዋና መስሪያ ቤት፣ ሪጅኖች፣ ቅ/ጽ/ቤቶችና መስክ ጽ/ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

## 5. የመመሪያው ዓላማ

ግልጽ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የንብረት አስተዳደር በማስፈን በኤጀንሲው መስሪያ ቤት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ

ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ ለማድረግ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የቋሚ ንብረት አስተዳደር

### 6. የቋሚ ንብረት አመዘጋገብ

1. በኤጀንሲው መስሪያ ቤት
   ሀ. ኤጀንሲው በስሩ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎችን ለእያንዳንዱ ንብረት የታሪክ ማህደር በመክፈት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀ ቅጽ መሠረት ወይም በኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት በመጠቀም መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡
   ለ. የተጠናቀረ መረጃ የያዘ የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ መያዙን የአቅርቦትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የመከታተልና የመቆጣጠር ሀላፊነት አለበት፡፡
   ሐ. የንብረቱ ተጠቃሚ ሰዎችን የንብረት ምዝገባ ካርድ መያዝ አለበት፡፡
   መ. ለእያንዳንዱ የኤጀንሲው ቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር መስጠት ያለበት ሲሆን፣ ይህ ቁጥር በቋሚ ንብረቱ ላይ መለጠፍ ወይም መጻፍ አለበት፡፡
   ሠ. የቋሚ ንብረት ካርዶችና የቋሚ ንብረት መዝገቦች ወቅታዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
   ረ. በየዓመቱ የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ማካሄድ አለበት፡፡ የቋሚ ንብረቶቹ ያሉበት አቋም ወይም የሚገኙበት ቦታ ላይ ማናቸውም ለውጥ ቢኖር ይኸው በቋሚ ንብረት ካርዱ፣ በቋሚ ንብረቱ መዝገብ እና በጠባቂዎች የንብረት ወይም የመጋዘን ኃላፊ ዝርዝር ውስጥ እንዲመለከት መደረግ አለበት፡፡
   ሰ. የማናቸውም ንብረት መጥፋት ወይም መኖሩ የማይታወቅ ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩ ለኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ተደርጎ ወዲያውኑ ምርመራ መካሄድ አለበት፡፡
   ሸ. የንብረት ቆጠራ ሲደረግ ያልተገኙ ወይም መኖራቸው ያልታወቀ ቋሚ ንብረቶች ሲያጋጥሙ ለኤጀንሲው የበላይ ሃላፊ ሪፖርት ይቀርባል፡፡ በምርመራውም ሪፖርት ጉዳዩ የወንጀል ድርጊት ያለው መሆኑ በማስረጃ ሲደገፍ ለህግ ጉዳዮች

ዳይሬክቶሬት ተላልፎ ክስ እንዲመሰረት ወይም ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ አለበት፣

ቀ. ዋጋቸው ከብር 1000 /አንድ ሺህ/ በታች ሆነው የአገልግሎት ዘመናቸው ከአንድ አመት በላይ የሆኑ ንብረቶች ለብክነት እንዳይጋለጡ ለብቻ መዝገቦ በመያዝ የወጪና ገቢ እቅስቃሴያቸው ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡

በ. ቋሚ ንብረት ለአንድ የሥራ ሂደት ወይም ሠራተኛ ወጪ ሆኖ ከተሰጠ በኋላ ወደ መጋዘን ሳይመለስ በዚያው ወደ ሌላ ሠራተኛ ወይም የሥራ ሂደት በርክክብ ከተላለፈ በስቶክ ያለው የቋሚ ንብረቱ መዝገብና ካርድ ቋሚ ንብረቱን በተረከበው አካል ወይም ሰራተኛ ስም መስተካከል አለበት፡፡

## 2. የኤጀንሲው የበላይ ሀላፊ ተግባርና ኃላፊነቶች

የኤጀንሲው የበላይ ሀላፊ፡-

ሀ. በኤጀንሲው ንብረት ክፍል የሚመደቡ ሠራተኞች በሙያው ወይም ተዛማጅነት ባለው የትምህርት ዘርፍ የሰለጠኑ መሆናቸውን እንዲረጋገጥ ማድረግ፣

ለ. የንብረት የሥራ ክፍል በማደራጀት በሰው ኃይል መሟላቱን የማረጋገጥ፣

ሐ. የኤጀንሲው ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጥ የጥገና ሥርዓት የመዘርጋት፣

መ. በኤጀንሲው ንብረት ላይ ጉድለት መታየቱ በኦዲተሮች ወይም በሌላ አካል ሲረጋገጥ ንብረቱ በምርመራው መሠረት በአይነት ወይም በገንዘብ እንዲተካ የማስደረግ፣

ሠ ዓመታዊ እና እንደአስፈላጊነቱ ድንገተኛ የንብረት ቆጠራ እና የስቶክ ምርመራ እንደንብረቱ አይነት የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ እንዲካሄድና ሪፖርት እንዲቀርብ የማድረግ፣

ረ. በንብረት ሽያጭ አፈፃፀም ሂደት ቅር የተሰኘ ገዢ የሚያቀርበውን አቤቱታ እንዲጣራና በጽሑፍ ምላሽ እንዲሰጠው የማድረግ፣

ሰ. በዚህ መመሪያ የተገለፁትን ሌሎች ተግባሮች በበላይነት መከታተልና ማስፈፀም፡፡

ኃላፊነትና ተግባር አለው፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት ሠራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

3. **የኤጀንሲው ንብረት ክፍል ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ. የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅንና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተዘጋጁ የግዥና የንብረት አስተዳደር ማንዋሎችን በመጠቀም ሙያው በሚጠይቀው ክህሎት የመስሪያ ቤቱን ንብረት ያስተዳድራል፣

ለ. የኤጀንሲውን ንብረት መረጃ አግባብ ባለው አዋጅና በዚህ መመሪያ በተገለጸው መሠረት አሟልቶ ይይዛል፣ በተጠየቀም ጊዜ ያቀርባል።

## 7. የቋሚ ንብረቶች መነሻ ዋጋ ወስኖ ስለመመዝገብ

1. የቋሚ ንብረቶች ዋጋ አተማመን

ሀ. የተገዙ ንብረቶች የመጀመሪያ ዋጋ የሚረጋገጠው በንብረት ካርዱ ላይ የተመዘገበውን የኢንቮይስ ዋጋ መሠረት በማድረግ ነው።

ለ. ያለፉት ግዥዎች ዋና ኢንቮይስ በማይገኝበት ጊዜ ኤጀንሲው የመጀመሪያውን ዋጋ የሚገምተው ተመሣሣይ ወይም አንድ አይነት ንብረቶች በተመሳሳይ ጊዜ የተገዙበትን ዋና ኢንቮይስ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

ሐ. ከላይ በተራ ቁጥር ሀ ወይም ለ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተሟልተው ካልተገኙ ዋጋው በግምት ተተምኖ ይሰራል።

2. ግንባታዎች፣

ሀ. ኤጀንሲው ያከናወናቸውን የግንባታ ሥራዎች እንደ ቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ መመዝገብ አለባቸው።

ለ. የኤጀንሲውን ህንጻዎች ለመስራት የተደረገን የቅድመ ግንባታ ቀጥተኛ ወጪዎች እና የአስተዳደርና ምክር አገልግሎት እና የመሣሰሉትን ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን በቋሚ ንብረት ካርድ መመዝገብ አለባቸው።

ሐ. በግንባታ ላይ የሚገኙ ሥራዎች የሚተመኑት የተጠናቀቁትን ሥራዎች የመተመኛ ስሌት ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

መ. ለሕንጻው የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ሕንጻውን ለመሥራት ወይም ለመግዛት የተደረገውን ጠቅላላ ወጪ በመነሻነት በመውሰድ ከዚሁ ሂሣብ ላይ በየዓመቱ

አምስት በመቶ በመቀነስ ይሆናል። ሕንጻውን ለመሥራት ወይም ለመግዛት የተደረገው ጠቅላላ ወጪ የማይታወቅ ከሆነ የሕንጻው ወቅታዊ የመተኪያ ዋጋ እንደመነሻ ይወስዳል።

ሠ. ሕንጻዎችን በሽያጭ ማስወገድ ሲፈለግ እንደቅደም ተከተላቸው የሚከተሉት ዘዴዎች በመጠቀም የሕንጻውን ዋጋ መተመን ይገባል፣

i. የግልጽ ገበያ አተማመን ዘዴ፡- ሕንጻው በግልጽ ጨረታ ቢሸጥ የሚኖረውን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ የሕንጻ ዋጋ ላይ መድረስ።

ii. የወቅቱ የመተኪያ ዋጋ ዘዴ፡- የሕንጻው ትክክለኛ ዋጋ የማይታወቅ ከሆነ በአሁኑ ጊዜ የተመሣሣይ ሕንጻ አጠቃላይ የግንባታ የመተኪያ ወጪ ግምት ውስጥ በማስገባት ግምት ይወሰዳል። ይህ ማለት ተመሣሣይ ሕንጻ በተመሣሣይ አካባቢና በተመሣሣይ ዕቃዎች አሁን ለመስራት ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ በማሰብ መከናወን ይኖርበታል።

iii. ኤጀንሲው በየጊዜው የሚያዘጋጀውን ግምታዊ ደረጃና የካሬ ዋጋ ወጪን መሠረት ባደረገ መስፈርት ተጠቅሞ የሕንጻዎቹን ዋጋ እንዲወጣ መደረግ አለበት፣

iv. ግምት ለሚሰሩ ባለሙያዎች ኮንትራት በመስጠት የሕንጻውን ዋጋ ማስላት ይቻላል።

3 የሌሎች ቋሚ ንብረቶች ዋጋ ስለመገመት

ሀ. የተሽከርካሪዎች ዋጋ የሚተመነው አዲስ የመተኪያ ዋጋን መነሻ በማድረግ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ለዚህ ዓላማ ያዘጋጀውንና በየዓመቱ አስር በመቶ የዋጋ ቅናሽ በማድረግ የማስላት ዘዴን በመጠቀም ይሆናል።

ለ. የቢሮ ዕቃዎች ዋጋ የሚተመነው ዕቃዎቹ ያሉበትን አቋም መሠረት ባደረገ መስፈርት ይሆናል።

ሐ. የቢሮ መሣሪያዎች ዋጋ የሚተመነው የመሣሪያዎቹን የአገልግሎት ዘመን በመስፈርትነት በመውሰድ ሲሆን ስሌቱ በየዓመቱ መሣሪያዎቹን አስር በመቶ (10%) የዋጋ ቅናሽ በማድረግ የሚሰላ ይሆናል

መ.የማይንቀሳቀሱ ወይም ሙሉ በሙሉ የተበላሹ ቋሚ ንብረቶች በመዝገብ ዋጋቸው (Book value) ይመዘገባሉ፡፡

4. በእርዳታ፣ በትውስት ወይም በስጦታ የተገኙ ንብረቶች

1. ኤጀንሲው በእርዳታ ወይም በስጦታ የሚያገኛቸውን ንብረቶች ዋጋ እና የአገልግሎት ዘመናቸውን የሚገልጽ መረጃ ከለጋሾች ወይም ከሰጡት አካላት መጠየቅ እና በቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርዱ ላይ ማመልከት አለባቸው፡፡ መረጃው ካልተገኘ በግምት ዋጋው መመዝገብ ይኖርበታል፡፡
2. በትውስት የተገኙ ንብረቶች ዋጋ እና የአገልግሎት ዘመናቸውን ከአዋሾች የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ ከኤጀንሲው የቋሚ ንብረቶች መዝገብ በተለየ የንብረት መመዝገቢያ ካርድ ላይ መመዝገብ አለባቸው፡፡ መረጃው ከአዋሾች ካልተገኘ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ 1 /ለ እና ሐ/ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 8. የቋሚ ንብረት የእርጅና ቅናሽ

በኤጀንሲው ቋሚ ንብረት ላይ የእርጅና ቅናሽ ማስላት ያስፈለገው የንብረቱን ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ሣይሆን አግባብነት ካለውና ሚዛናዊ ከሆነ ዋጋ ላይ ለመድረስ ነው፡፡ የቋሚ ንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ የሚታወቀው ሲሸጥ በሚገኝ የገበያ ዋጋ ብቻ ይሆናል፡፡ ስለሆነም፣-

ሀ. ንብረት መዝገብ ላይ ያለ የእርጅና ቅናሽ ዋጋ ንብረትን ለማስወገድ መነሻ ግምት ሆኖ ሊወሰድ አይችልም፣

ለ. የኤጀንሲው ንብረት ክፍል በየዓመቱ መጨረሻ ላይ የቋሚ ንብረት የእርጅና ቅናሽን በማስላት የንብረቱን የመዝገብ ዋጋ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፣

ሐ የእርጅና ቅናሽ የሚሰራው ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴን በመጠቀም ይሆናል፡፡

መ. የቋሚ ንብረት የእርጅና ቅናሽን የማስላትና በመዝገብ ላይ የመመዝገብ ኃላፊነት የኤጀንሲው ንብረት ክፍል ይሆናል፣

ሠ. በበጀት ዓመቱ መካከል ለተገዙ ቋሚ ንብረቶች የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው ንብረቱ ከተገዛበት ዕለት አንስቶ ይሆናል፡፡

ረ. ኤጀንሲው የቋሚ ንብረት የእርጅና ቅናሽ (Depreciaion) አሠራር ሥርዓት ሲዘረጋ የኤጀንሲውን ፋይናንስ ክፍል ከኤጀንሲው ንብረት ክፍል የቋሚ

ንብረት የእርጅና ቅናሽ ዋጋ ሲደርሰው ሂሣቡን በሂሣብ መዝገብ ላይ ይመዘግባል፡፡

ሰ. በቋሚ ንብረቱ የመጨረሻ የእርጅና ቅናሽ ዘመን ከዓመቱ የእርጅና ቅናሽ ላይ ብር 10 /አስር ብር/ ተቀንሶ የንብረቱ የመዝገብ ዋጋ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ሸ. ዋጋውን በእርጅና ቅናሽ ላይ ለጨረሰ ንብረት የእርጅና ቅናሽ አይታሰብም፡፡

ቀ. ዋጋውን በእርጅና ቅናሽ የጨረሰ ንብረት የጥገና ወጪ የዚያ አመት ወጪ እንጂ የንብረቱ ዋጋ ተደርጎ አይወሰድም፡፡

## ክፍል ሶስት
## የስቶክ አስተዳደር ሥርዓት

### 9. የስቶክ ቁጥጥር ሥርዓቶች

1. የስቶክ ቁጥጥር ሥርዓት በኤጀንሲው መዘርጋት ያለበት ሲሆን በስቶክ የሚቀመጡ ዕቃዎች ለጤና አደገኞች ወይም ባላቸው ዋጋና በቀላሉ የመንቀሳቀስ ባህርይ ምክንያት ለሥርቆት የሚጋለጡ ናቸው ተብሎ ሲታመን ልዩ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

2. የኤጀንሲው የስቶክ ቁጥጥር ሥርዓት የሚከተሉትን መሠረታዊ መርሆዎች ያገናዘበ መሆን አለበት፡-

ሀ. የስቶክ ቁጥጥር አስተማማኝ፣ ተገቢና መሠረታዊ የስቶክ መዛግብቶችን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡እነዚህ የስቶክ መዛግብት በተለምዶ የስቶክ ካርዶች እና ቢን ካርዶች በመባል ይታወቃሉ፡፡

ለ. የዕቃዎች መቀበያና ማውጫ ሰነዶች የሚገኙበት መንገድ ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሆነው አስቀድመው የታተሙና ተከታታይ ቁጥሮች ያሉዋቸው መሆን አለባቸው፡፡

ሐ. ከዚህ በላይ የተመለከቱት ቫውቸሮች ንብረት ገቢ ወይም ወጪ ከተደረገባቸው በኋላ በተቻለ ፍጥነት በዋናው የስቶክ መዛግብቶች ላይ ማሻሻያ መደረግ አለበት፡፡

መ. የንብረት መጉደል ወይም መጭበርበር ተከስቷል የሚል ጥርጣሬ ሲኖር ንብረቱ ከመቀበል ጀምሮ ማውጣትን፣ ጥቅም ላይ ማዋልንና አግባብ ያለው ሆኖ ሲገኝ እስከ ማስወገድ ድረስ ያለውን እንቅስቃሴ ወደ ኋላ ሄዶ የታተሙት ሰነዶች ቁጥራቸው ተከታታይና ይዘታቸው ያልተደለዘ ወይም ለውጥ ያልተደረገባቸው መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡

## 10. የስቶክ አስተዳደር

ኤጀንሲው ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁለት የሥራ መደቦች ላይ በሚገኙ ሠራተኞች መካከል በቂ የሃላፊነት መነጣጠል መደረጉን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ. የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ሃላፊነቶች ለአንድ ሠራተኛ መስጠት የለባቸውም፡፡

ለ. በተመሣሣይ ስቶክ የማዘዝ፣ የመረከብ፣ ክፍያን የመፍቀድና ግዥን የማከናወን ሃላፊነቶች መለያየት አለባቸው፡፡

## 11. መሠረታዊ የስቶክ መዛግብቶች

1. የኤጀንሲው ንብረት ክፍል የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባዘጋጃቸው ቅጾች በመጠቀም የስቶክ መረጃዎችን መያዝ አለባቸው፡፡
2. የኤጀንሲው ንብረት ክፍል የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በመከተል በሚዘጋጅ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የስቶክ መረጃን መያዝና ማስተዳደር ይችላሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የኤጀንሲውን የስቶክ መረጃዎችን በተለየ ሁኔታ መያዝ አስፈላጊና የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በማቅረብና በማስፈቀድ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀ ቅጽ /ፎርም/ መጠቀም ይቻላል፡፡

## 12. ስቶክ ስለመቀበል

የኤጀንሲው ንብረት ክፍል አዲስ ስቶክ ሲቀበል በሚከተሉት ላይ ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ሀ. የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው ዕቃውን ለመረከብ የሚያስችል ከሚመለከተው የሥራ ክፍል የተሰጠ ትዕዛዝ መኖሩን፣

ለ. የዕቃ ግምጃ ቤት ሃላፊው የዕቃውን ትክክለኛነት ከተሰጠው ትዕዛዝ የዕቃ ዝርዝር (specification) ጋር በማመሣከር ወይም ባለሙያ የሚፈልግ ከሆነም በባለሙያ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ማግኘት፣

ሐ. ስቶኩ የተገኘው ሌሎች የሥራ ክፍሎች ወይም ስቶኩን ከሚመልሱ ሰራተኞች ሲሆን የተገኘው ስቶክ ወጪ ከተደረገበት በሌላ የሥራ ክፍል ከተዘጋጀው የንብረት ወጪ ማድረጊያ ሰነድ ጋር ማመሣከር፣

መ. የስቶክ ክፍል ኃላፊ ከማናቸውም ምንጭ ንብረት ሲገኝ የስቶኩን መዝገብ ንብረቱን በተቀበለበት ዕለት የማስተካከል፣

## 13. ከመጋዘን ስቶክን የማውጣት ሥርዓት:-

1. ስቶክ ከመጋዘን የሚወጣው መጀመሪያ የገባው መጀመሪያ ይወጣል ( FIFO) የሚለውን የሂሣብ አሠራር መሠረት በማድረግ ነው። ሆኖም ከዚህ የተለየ ዘዴ መጠቀም ግዴታ ከሆነ የአቅርቦትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በሚያቀርበው ሀሳብ መሰረት ለዋና ዳይሬክተሩ ቀርቦ ይወሰናል፡፡ ስቶክ ከመጋዘን ሲወጣ፡-
   ሀ. የስቶክ ክፍል ኃላፊ በዋናው የስቶክ መዝገብ ላይ ተገቢውን ማቀናነሻ መደረጉን ለእያንዳንዱ ሠራተኛ የስቶክ ዝርዝር ተመዝግቦ መያዙን ማረጋገጥ አለበት።
   ለ. የስቶክ ወጪ መጠየቂያ ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች ወይም ሠራተኞች ለስራ የሚያስፈልጋቸውን ንብረት በሚፈልጉበት ወቅት የዕቃ መጠየቂያ ቅጽ በተገቢው ሁኔታ በመሙላትና በሚመለከተው ኃላፊ በማስፈረም የስቶክ አስተዳደር ተግባርን ለሚያከናውን የሥራ ክፍል ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
   ሐ. የስቶክ ወጪ ጥያቄን በማረጋገጥ የስቶክ ንብረት የሚያስተዳድረው የሥራ ሂደት የተጠየቁት ዕቃዎች ወይም ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ያሉ መሆናቸውን በማጣራት ለኃላፊው በማቅረብ ያስወስናል።

መ. የተጠየቀ የስቶክ ዕቃን ወይም ንብረትን ለመረከብ/ወጪ ለማድረግ የተጠየቀው ዕቃ ወይም ንብረት በንብረት መረከቢያ ቅጽ ላይ በተገቢው ሁኔታ ተሞልቶና በተረካቢው ተረጋግጦ ወጪ መደረግ አለበት፡፡

ሠ. ንብረት ከመጋዘን ወጥቶ ከኤጀንሲው ውጪ ሲሰራጭ ወይም ሲወገድ ወይም ሲሸጥ የኤጀንሲው ንብረት ክፍል ኃላፊ በተረጋገጠ የዕቃ ማውጫ ቅጽ መሠረት ወይም የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ሥርዓት በመጠቀም በተረጋገጠው መሠረት መሆን አለበት፡፡

## 14. የስቶክ ቆጠራ አፈጻጸም

1. ስቶክ ቆጠራ መደረግ ያለበት ከመጋዘን ወይም ከስቶክ መዛግብት ሥራ ገለልተኛ በሆኑ ሠራተኞች ነው፡፡ የስቶክ ቆጠራው የሚደረገው የንብረትና የፋይናንስ ተግባራትን ከሚያከናውኑ የሥራ ሂደቶች በሚቋቋም ኮሚቴ ይሆናል፡፡
2. የስቶክ ቆጠራ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መካሄድ አለበት፡፡ ሆኖም በኤጀንሲው የስርቆት ሪፖርት ሲቀርብ ወይም አዲስ ሠራተኞች ሲመደቡ እና በአመት ከአንድ ጊዜ በላይ ስቶክ ቆጠራው መካሄድ አለበት ብሎ ሲታመን ስቶክ ቆጠራ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊያካሂድ ይችላል፡፡
3. የስቶክ አስተዳደር ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ሂደት ኃላፊ የኮሚቴው አባል ባይሆንም የስቶክ ቆጠራ ሥራን ለማቀላጠፍ መገኘት አለበት፡፡
4. ኮሚቴው ቆጠራውን ለማካሄድ እንዲችል የሚረዱ የተሟሉ ሁኔታዎች መኖራቸውን የኤጀንሲው ንብረት ኃላፊ ማረጋገጥ አለበት፡፡
5. ከቆጠራ በኋላና በየእለቱ ስለተቆጠረው እቃ ወይም ንብረት ካስቆጣሪው ጋር የመተማመኛ ፎርም መፈራረም ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

## 15. በስቶክ ቆጠራ ሪፖርት ስለማቅረብና በተገኙ ልዩነቶች ላይ ምርመራ ስለማካሄድ

1. የስቶክ ቆጠራውን የሚያካሂደው ኮሚቴ የቆጠራውን ዝርዝር ሪፖርት ለንብረት ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡
2. የስቶክ ቆጠራው ሪፖርት በስቶክ መዝገቡ፣ በዕቃዎች መቀበያ ሰነድ፣ በስቶክ መጠየቂያ እና በስቶክ ማውጫ ሰነድ እና በትክክለኛው ቀሪ ስቶክ መካከል የታዩትን ማናቸውም ልዩነቶች በዝርዝር መግለጽ አለበት፡፡ ልዩነቶች ከታዩም በዚህ መመሪያ መሠረት ንብረቱ እንዲተካ ይደረጋል፡፡

## 16. የተለዩ ዕቃዎችን ስለመቆጣጠር

1. በመጋዘን የተቀመጡ አንዳንድ ዕቃዎች በጠቅላላ ለሕዝብ ጤና አደገኛ የሆኑ ወይም ጉዳትን የሚያስከትሉ የጦር መሣሪያዎች፣ መድሐኒቶች፣ ኬሚካሎች እና የመሣሰሉት ካላቸው ልዩ ተፈጥሮ የተነሣ ቢበዛ በየ3 /ሶስት/ ወሩ መቆጠር አለባቸው፡፡
2. ውድ ዋጋ ያላቸው በቀላሉ ሊወሰዱ የሚችሉ ዕቃዎች እና በፍጥነት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ዕቃዎች ድንገተኛ ቆጠራ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡
3. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በዓመት እስከ አራት ጊዜ የልዩ ዕቃዎች ድንገተኛ ቆጠራ እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል፡፡

## 17. የስቶክ መጠንን ስለመቆጣጠር

የስቶክ አስተዳደር ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ሂደት በየጊዜው የሚያስፈልጉ ስቶኮችን በበቂ መጠን መያዝ ይኖርበታል፡፡ ምን ያህል የስቶክ መጠን እንደሚያስፈልግ ለመወሰን ለመደበኛ ሥራ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉ የስቶክ ፍላጎቶችን፣ የታዘዙ ዕቃዎች መጋዘን ለመድረስ የሚፈጅባቸውን ጊዜ፣ የመጋዘኑ የመያዝ አቅም እና የግዥ ትዕዛዙን ለመፈፀም የሚያስፈልገውን ወጪ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

## 18. የንብረት አጠቃቀምና ጥገና

1. የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ የመስሪያ ቤቱን ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢ የጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡
2. ለማሽነሪዎች /መሣሪያዎች/፣ ለተሽከርካሪዎች፣ ሕንጻዎችና ለሌሎች ንብረቶች መሠረታዊ የሆነ ጥገና ንብረቶቹ የሚኖራቸውን የአገልግሎት ዘመን ያራዝማል ተብሎ ሲታመን ወጪው አስቀድሞ በቋሚ ንብረት በተመዘገበው ሂሣብ ላይ ተጨምሮ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አራት
# የኤጀንሲው ንብረት አወጋገድ

## 19. ቋሚ ንብረትን የማስወገድ ስልጣን

ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ መሠረት ቋሚ ንብረቶችን የማስወገድ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## 20. የኤጀንሲውን ንብረት ስለማስወገድ

1. ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች ንብረትን ማስወገድ ይችላል፡፡
   - ሀ. ንብረቱ ለኤጀንሲው ዓላማዎች የማይፈለግ ሲሆን፣
   - ለ. ንብረቱን ይዞ መቀጠል የሚያስከትለው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ የማያዋጣ ሲሆን፣
   - ሐ. በልዩ ልዩ ምክንያት ንብረቱ የሚፈለግበትን አገልግሎት በብቃት መስጠት የማይችል ወይም ከአገልግሎት ውጪ ሲሆን፣
   - መ. ኤጀንሲው ከሚኖረው የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ዕቅድ አንጻር ትርፍ መሆኑ ሲታመን፣

2. ኤጀንሲው ከላይ በተገለፀው መልኩ የማይፈለጉ ንብረቶችን፣ ተሸከርካሪዎችንና፣ ብረታብረቶችን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 (3) በተመለከተው መሰረት በወቅቱ ያስወግዳል፣ ሆኖም ተሽከርካሪዎችንና፣ ብረታብረቶችን ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በማስተላለፍ ተሸጦ ገንዘቡ ለኤጀንሲው ገቢ እንዲሆን ማድረግ ይችላል፡፡

3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም የአቅርቦትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ኤጀንሲው በሽያጭ እንዲወገዱ ስለሚፈልጓቸው ግምታቸው ከብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ በላይ ስለሆኑ ንብረቶች በየጊዜው ዝርዝር መረጃ ለኢንቨስትመንትና ፈንድ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ አለበት፡፡

## 21. ንብረት የማስወገድ ሂደትና ኃላፊነት

ኤጀንሲው ንብረቶችን ለማስወገድ የሚከተለውን ሂደት መከተል ይኖርበታል፡፡

1. የኤጀንሲው ንብረት ክፍል የሚወገድ ንብረት ዝርዝርን በቅጽ ሞልቶ ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊ በወቅቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊ የቀረበለትን መጠየቂያ ቅጽ መርምሮ ለንብረቶች አስወጋጅ ኮሚቴ ይመራል፡፡
3. የኤጀንሲው ንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የተመራለትን መጠየቂያ ቅጽ መርምሮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አስፈላጊውን ይፈጽማል፡፡
4. የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊ ከንብረት ሽያጭ ውጤት በስተቀር ከንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የቀረበለትን የውሣኔ ሃሳብ ያጸድቃል፡፡እንዲወገዱም ውሣኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች በወቅቱ መወገዳቸውን እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡

## 22. ንብረት የማስወገድ ሥርዓቶች

3. የኤጀንሲው ንብረት ክፍል ንብረት እንዲወገድ ለምን እንዳስፈለገ ለይቶ የማወቅ ሃላፊነት አለበት፡ በተጨማሪም ንብረት ሲያስወግድ፣-

ሀ. የንብረቱ ሕጋዊ ባለቤት ማን እንደሆነ መለየትና የኤጀንሲዉ ንብረት እንደሆነ ማረጋገጥ፣

ለ. ሕንጻና ተመሣሣይ ግንባታዎች የባለቤትነት መብት የኤጀንሲው በመሆኑ እነዚህን ንብረቶች ማስወገድ ሲያስፈልግ እንዳስፈላጊነቱ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርን ማማከር፣ እና

ሐ. የሚወገዱት ንብረቶች ልዩ ጠቀሜታ ያላቸው ወይም ጉዳት የሚያስከትሉ ሲሆኑ አግባብ ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ጋር መነጋገር ይኖርበታል። የሚወገዱት ንብረቶች በባህሪያቸው ለጤና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎች ወይም መድኃኒቶች ወይም የጨረር ጉዳት የሚያስከትሉ ሆነው ሲገኙ በአወጋገዱ ላይ አስፈላጊውን እገዛ ከሚመለከተው አካል ትብብር ሊጠየቅ ይችላል።

2. የሚወገደውን የኤጀንሲው ንብረት የመነሻ ዋጋ መገመት

ሀ. እንዲወገድ የተወሰነበትን የእያንዳንዱን የኤጀንሲውን ንብረት የወቅቱን የመነሻ ዋጋ ንብረቱን በሚያስተዳድረው የሥራ ሂደት ይገመታል።

ለ የአቅርቦትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች ሙያው ያላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የመነሻ ዋጋውን አገማመት በተመለከተ እንዲያማክሩት ሊጠይቅ ይችላል።

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ መሠረት የሚጠየቀው የሙያ ምክር ከንብረቱ ልዩ ባህሪ የተነሣ የንብረቶቹን አጠቃቀም በተመለከተ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸውን የመንግሥት ተቋማት ወይም በዚህ ሙያ የተሠማሩ ድርጅቶችን ወይም ግለሰቦችን መሆን ይኖርበታል።

መ. የመነሻ ዋጋን የገመተ ግለሰብ በሽያጭ ወይም በአወጋገድ ሥራው መሳተፍ የለበትም።

3. የኤጀንሲውን ንብረት የማስወገጃ ዘዴዎች

የኤጀንሲውን ንብረት ለማስወገድ የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮችን አንዱን በመጠቀም ይሆናል፡፡

ሀ. ለሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት በማዛወር ወይም በማስተላለፍ፣

ለ. ባለበት ሁኔታ ለሕዝብ በጨረታ ወይም በሐራጅ በመሸጥ፣

ሐ. ንብረቱን ፈትቶ በመለዋወጫነት ጥቅም ላይ በማዋል ወይም በመሸጥ፣

መ. ንብረቱን በውዳቂነት ማስወገድ፣

ሠ. ንብረቱን በስጦታ በመስጠት ማስወገድ፣

ረ. ንብረቱን በመቅበር ወይም በማቃጠል ማስወገድ፡፡

## 23. ንብረት ለሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት በማስተላፍ ስለማስወገድ

1. ንብረትን ለሕዝብ በሐራጅ ወይም በጨረታ መሸጥ የሚያስከትለው ወጪ የሚታወቅ ስለሆነ ኤጀንሲው ለማስወገድ የፈለገውን ንብረት ወደ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ለማዛወር ይቻል እንደሆነ በቅድሚያ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡
2. በኤጀንሲውና በመንግስት መስሪያ ቤቶች መካከል የሚደረገው የንብረት ዝውውር የሚፈጸመው የወቅቱን የንብረቱን ዋጋ ግምት በመመዝገብ መሆን አለበት፡፡

## 24. ንብረቱን ባለበት ሁኔታ ለሕዝብ በጨረታ ወይም በሐራጅ መሸጥ

1. የኤጀንሲውን ንብረት በጨረታ ወይም በሐራጅ ለመሸጥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች፣

ሀ. የአቅርቦትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የኤጀንሲውን ንብረት በዚህ መመሪያ የተገለጸውን የንብረት ማስወገድ አሰራር በመከተል በጨረታ ወይም በሐራጅ በመሸጥ ማስወገድ ይችላል፡፡

ለ. የአቅርቦትና ጠቅላላ አገልግሎት የተሻለ ዋጋ ለማግኘት፣ በፍጥነት ሽያጩን በመፈፀምና የሚያስከትሉትን ችግሮች በመገምገም የተሻለውን የመሸጫ ዘዴ መምረጥ ይኖርበታል፡፡

ሐ. የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ለጨረታ ወይም ለሐራጅ የሚቀርቡትን ዕቃዎች የመነሻ ዋጋ የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊ እንዲያጸድቀው ማቅረብ አለበት፡፡

መ. ተፈትተው እንዲሸጡ የተወሰነባቸውን መለዋወጫዎች፣ እንዲሁም ውዳቂ ብረታ ብረቶች የጨረታ ወይም የሐራጅ መነሻ ዋጋ የመለዋወጫውን ወይም የብረታ ብረቱን ዓይነት፣ የገበያውን ሁኔታና ሌሎች መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የተገመተ መሆን አለበት፡፡

ሠ. ወጪን ለመቀነስ ሲባል የሚሸጠውን ንብረት በአንድ ጊዜ በጥቅል መሸጥ አለበት፡፡

ረ. የሽያጭ ማስታወቂያው ዘዴ የሚከተሉትን ታሣቢ ማድረግ አለበት፡፡

i. የሚሸጠው ንብረት የመነሻ ዋጋ ከብር 10,000 /አስር ሺህ/ ያነሰ ከሆነ ኤጀንሲው ሽያጩን ቢያንስ ለ7 ተከታታይ ቀናት በሕዝብ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለሁለት ጊዜ እንዲወጣ ማደረግ አለበት፡፡

ii. የሚሸጠውን ንብረት ዋጋ ከብር 10,000 /አስር ሺህ/ በላይ ከሆነ ኤጀንሲው በታወቀና ሰፊ ተነባቢነት ባለው ጋዜጣ ቢያንስ ለ1 ጊዜ ማስታወቂያው ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

iii. ከላይ በተራ ቁጥር (i) እና (ii) በተጠቀሰው መንገድ ሽያጩ ካልተወሰነ የንብረት አስወጋጅ/ሽያጭ ኮሚቴ ንብረቱ የሚወገድበትን ሌላ አማራጭ ዘዴ ለበላይ ኃላፊው በማቅረብ ሲወሰን ንብረቱ እንዲወገድ ያደርጋል፡፡

**2. በጨረታ ስለሚደረግ ሽያጭ**

ሀ. ኤጀንሲው የሚያወጣው የጨረታ ማስታወቂያ ለዚህ ዓላማ በኤጀንሲው በተዘጋጀ ቅጽ መሰረት ይሆናል፡፡

ለ. ተጫራቾች እንዲጫረቱ የሚሰጠው ጊዜ ከ15 እስከ 30 ቀናት ባለው ጊዜ ሆኖ በኤጀንሲው ንብረቶች አስወጋጅ ኮሚቴ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሐ. ኤጀንሲው በጨረታ ማስታወቂያው እስከተመለከተው ጊዜ ድረስ ክፍት ሆኖ የሚቆይ የተለየ የጨረታ ሣጥን ማዘጋጀት አለበት፡፡ አስወጋጅ ኮሚቴውም ጊዜው ሲደርስ የጨረታ ሣጥኑን ማሸግ አለበት፡፡ ማናቸውም ለጨረታው ማቅረቢያ የተሰጠው ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚቀርቡ የጨረታ ሰነዶች ሳይከፈቱ ለተጫራቾቹ መመለስ አለባቸው፡፡ በጨረታ ሽያጭ በቂ ተወዳዳሪ ካልቀረበ ወይም የቀረበው ዋጋ ተቀባይነት ካላገኘ መስሪያ ቤቱ የጨረታውን ማስታወቂያ በድጋሚ የማውጣት ወይም ጨረታውን በመሠረዝ ሌላ የማስወገጃ አማራጭ የመጠቀም መብት አለው፡፡

መ. ኤጀንሲው ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ እንዲያስይዙ መጠየቅ ያለበት ሲሆን፣ ለእያንዳንዱ በጨረታ መከናወን ላለበት ሽያጭ የጨረታ ማስከበሪያ ሊኖር እንደሚገባ መወሰን አለበት፡፡ የሽያጭ ኮሚቴውም ለእያንዳንዱ ሽያጭ የሚያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ በጨረታው ያሸነፈው ተጫራች እንደተመረጠ ወዲያወኑ ጨረታውን ላላሸነፉ ተጫራቾች መመለስ አለበት፡፡

ሠ. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው እና የሽያጭ ኮሚቴ አባላት ባሉበት ግልጽ ሆኖ መከፈት አለበት፡፡ የተጫራቾች ስምና የመጫረቻዉ ዋጋ በሽያጭ ኮሚቴ አስተባባሪ መነበብ አለበት፣ የሽያጭ ኮሚቴ ፀሐፊም ይህንኑ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

ረ. ኮሚቴው የትኛውን የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ መቀበል እንዳለበት ይወስናል፡፡ ከፍተኛው ጨረታ በመነሻነት በተያዘው ዋጋ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ኮሚቴው ከፍተኛውን የጨረታ ዋጋ ሊቀበል ይችላል፡፡

ሰ. የሽያጭ ኮሚቴው በጨረታው የደረሰበትን ሂደት ለንብረት ሽያጩ አፀዳቂ ኮሚቴ እንዲያፀድቀው ማቅረብ አለበት፡፡

3. በሐራጅ ስለሚደረግ ሽያጭ

ሀ. ኤጀንሲው የሚያወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀ ቅጽ መሰረት ይሆናል፡፡

ለ. የሐራጁ መሪ ሐራጁ ከመጀመሩ በፊት የመነሻውን ዋጋ መግለጽ አለበት፡፡ በሐራጁ የመነሻው ዋጋ ወይም ከዚህ በላይ ንብረቱን የሚገዛ ካልተገኘ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የተሻለ ነው የሚለውን የማስወገጃ ዘዴ መምረጥ አለበት፡፡

4. የተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ማስወገጃ መመዘኛዎች

ኤጀንሲው ተሽከርካሪዎችንና መሣሪያዎችን ለማስወገድ ከሚከተሉት መመዘኛዎች ቢያንስ አንዱ መሟላቱን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

ሀ. በከፍተኛ ጉድለት ምክንያት ሊጠገን የማይችል ሲሆን፣

ለ. የመለዋወጫ ዕቃ በገበያ ላይ አለመገኘት፣

ሐ. ለማደስ የሚያስፈልገው ወጪ ከመተኪያ ዋጋው ጋር ሲነጻጸር መተካቱ የሚመረጥ ሲሆን፣

መ. በቴክኖሎጂ ኋላቀርነት ምክንያት ምርታማነቱ ዝቅተኛ ሲሆን፣

ሠ. ኤጀንሲው ከሚኖረው ወቅታዊም ሆነ የቅርብ ጊዜ የሥራ ዕቅድ አንጻር ትርፍ መሆኑ ሲታመን፣

ረ. አገልግሎት በሰጠባቸው ጊዜያት ለጥገና የወጣው ጠቅላላ ወጪ ከሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ ሳይሆን ሲቀር፣

ሰ. በእርጅና ምክንያት አገልግሎት መስጠት የማይችል ሲሆን፣

5. ቋሚ ንብረቶችን በጨረታ ሽያጭ ለማስወገድ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

ሀ. ቋሚ ንብረቱ በንብረትነት የተገኘበትን የሚገልጽ መረጃ ማጣራት፣

ለ. የቅድሚያ ግመታና ሽያጭ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ሁለት ኮሚቴዎችን ማቋቋም /የገማችና የሽያጭ ኮሚቴዎችን/፣

ሐ. የጨረታ ሰነዶችን በማዘጋጀት ጨረታ ማውጣት፣ ማጫረት፣ ጨረታውን መገምገምና ለንብረት ሽያጭ ጨረታ አጽዳቂ ኮሚቴ ሪፖርት ማቅረብ፣

ነ. የሽያጭ ገንዘቡን ወደ ኤጀንሲው የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ እና ንብረቱን ማስረከብ፣

ሠ. ተሽከርካሪን በሚመለከት የስም ዝውውሩ ለአሽናፊው እንዲፈጸም ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ማስታወቅ፡፡

ረ. በሽያጭ የሚወገደው ንብረት ተሽከርካሪ ከሆነ ጨረታው ከመውጣቱ በፊት የባለቤትነት ማስረጃ መኖሩንና የቦሎ ግብር የተከፈለ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

6. የተሽከርካሪዎች፣ የመሣሪያዎች እና የሌሎች ቋሚ ንብረቶች የጨረታ መነሻ ዋጋ

ሀ. ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች በልዩ ልዩ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ ሲሆኑ ወይም በብቃት አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ደረጃ ሲደርሱ በኤጀንሲው በተዘጋጀው የስሌት ዘዴ (formula) መሠረት የጨረታ መነሻ ዋጋቸውን በማስላት ማወቅና እንዲወገድ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ሌሎች ቋሚ ንብረቶችን በወቅቱ የገበያ ዋጋ በመገመት ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡

ለ. ሌሎች ቋሚ ንብረቶችን በወቅቱ የገበያ ዋጋ በመገመት መወገድ ይኖርባቸዋል««

7. ተሽከርካሪን ወይም መሣሪያን ባለበት ሁኔታ መሸጥ

እንዲወገድ የተወሰነበትን ተሽከርካሪ ወይም መሣሪያ ባለበት ሁኔታ ለመሸጥ ከዚህ በታች ከተመለከቱት ውስጥ ቢያንስ አንዱ መሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ. ተሽከርካሪው ወይም መሣሪያው የማይሰራ ከሆነ፣

ለ. ተሽከርካሪው ወይም መሣሪያው የማይሠራ ቢሆንም ሞተር፣ ትራንስሚሽን፣ ሻንሲ፣ አካሉ እና ሃይድሮሊክ ሲስተም በሙሉ ያሉ ከሆነ፣

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7/ለ/ ላይ የተመለከቱት ዋና ዋና አካላቱ የተሟሉ ባይሆንም የተሽከርካሪው ወይም የመሣሪያው ቀሪ አካል በገበያ ላይ ተፈላጊ መሆኑ ከተረጋገጠ፣

25. ንብረቱን ፈትቶ በመለዋወጫነት ጥቅም ላይ ማዋል ወይም መሸጥ

1. የኤጀንሲው አቅርቦትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የአንድን ንብረት አካላት ፈትቶ በመለዋወጫነት መጠቀም ወይም መሸጥ የሚችሉት ንብረቱን ባለበት



የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

ሁኔታ መሸጥ የማይቻል ሲሆን ወይም ባለበት ሁኔታ ከመሸጥ ይልቅ ፈትቶ መጠቀም ወይም መሸጥ የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ ሲሆን ነው፡፡

2. በመለዋወጫነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲሸጡ ከተወሰነባቸው ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ላይ ጠቃሚ አካሎችን ፈትቶ አግባብ ባለው የዕቃ አስተዳደር አሠራር መሠረት ገቢ እንዲሆኑና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም በጨረታ እንዲሸጡ ማድረግ ይቻላል፡፡

3. ተፈትተው እንዲሸጡ የተወሰነባቸው መለዋወጫዎች የጨሬታ መነሻ ዋጋ የመለዋወጫውን ዓይነት፣ የገበያውን ሁኔታና ሌሎች መረጃዎች መሠረት በማድረግ ይገመታል፡፡

## 26. ንብረቱን በውዳቂነት ስለማስወገድ

1. ከማናቸውም የንብረት ማስወገድ ሂደት የሚገኘው ገቢ ለማስወገድ የሚደረገውን ወጪ የማይሸፍን ነው ተብሎ ሲገመት ንብረቱ በውዳቂነት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴው የተሻለ ስለሚሆነው ዘዴና ማናቸውንም ከውዳቂው ሊገኝ የሚችለውን የሽያጭ ገቢ በሚመለከት ምክር ይሰጣል፡፡ በውዳቂነት እንዲወገዱ የሚደረጉ ሁሉ በኤጀንሲው የበላይ ሃላፊ መጽደቅ አለባቸው፡፡

2. ጠቃሚ አካሎቻቸው የተወሰዱባቸው ቀሪ ብረታ ብረቶች እና ውዳቂ ብረታ ብረቶች የመነሻ ዋጋ የገበያውን ሁኔታና ሌሎች መረጃዎች መሠረት በማድረግ መገመት አለበት፡፡

3. በውዳቂ ብረታ ብረትነት እንዲወገዱ የተወሰነባቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች እንዲሁም ተፈትተው ጠቃሚ አካሎቻቸው የተወሰዱባቸው ቀሪ ብረታብረቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም በጨረታ እንዲሸጡ ይደረጋል፡፡

4. ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመሆን ሥነ ምህዳርን በማይጎዳ ሁኔታ ውዳቂ ንብረቶችን በማቃጠልና በመቅበር ማስወገድ ይቻላል፡፡

## 27. ንብረትን በስጦታ በመስጠት ስለማስወገድ

1. ኤጀንሲው አንድን ንብረት ለሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም በማህበራዊ አገልግሎትና ልማት ተግባራት ላይ ለተሰማሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ለክልል መንግሥታት በስጦታ ሊያስተላልፍ የሚችለው ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

    ሀ. ንብረቱ ለኤጀንሲው ሥራ የማይውል ሲሆን፣

    ለ. ንብረቱ እንዲወገድ ቢደረግ የሚገኘው ገቢ ንብረቱን ለመሸጥ ወይም ለመጠበቅ ከሚወጣ ወጪ በጣም አነስተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

    ሐ. ንብረቱ የሚተላለፍለት አካል በንብረቱ በመጠቀም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ያግዛል ተብሎ በመስሪያ ቤቱ ሲታመን፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለፀው መሠረት ንብረት ለሌላ አካል በስጦታ እንዲተላለፍ የሚደረገው በኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ሲፈቀድ ብቻ ነው፡፡

## 28. ንብረቱን በመቅበር ወይም በማቃጠል ማስወገድ

ምንም ጠቀሜታ የሌላቸው ውዳቂ ንብረቶችን ኤጀንሲው በራሱ ወይም የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላትን በማማከር በመቅበር ወይም በማቃጠል ወይም በሌላ መንገድ ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንንም

1. የሚወገደው ንብረት ምንም ዓይነት የስነምህዳር ወይም የጤና ችግር የማያስከትል ከሆነ ኤጀንሲዉ በራሱ ኃላፊነት ንብረቶቹን ለይቶ በመቅበር ወይም በማቃጠል ማስወገድ ይችላል፡፡

2. የሚወገደው ንብረት ከፍተኛ የሥነምህዳር ወይም የጤና ችግር የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ኤጀንሲው ስለአወጋገዱ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመመካከር ንብረቱን በተገቢው መንገድ ማስወገድ ይኖርበታል፡፡

## 29. የኤጀንሲው ንብረቶች አስወጋጅ /ሽያጭ ኮሚቴ አወቃቀር፣ ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 5/ለ መሠረት የሚቋቋመው የንብረት አስወጋጅ/ሽያጭ ኮሚቴ:-

1. አወቃቀርና የስብሰባ ሥርዓት

ሀ. ኮሚቴው ከሶስት ያላነሱ አባላት ይኖሩታል፡፡

ለ. የኮሚቴው አስተባባሪ፣ አባላትና ፀሐፊ በኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ ይሰየማሉ፡፡

ሐ. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

መ. የኮሚቴው ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፡፡ የኮሚቴው ድምጽ እኩል ሲሆን አስተባባሪው ያለበት ወገን ወሣኝ ጽምጽ ይኖረዋል፡፡

ሠ. የኮሚቴው የአገልግሎት ዘመን ሶስት አመት ይሆናል፡፡ ሆኖም የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የኮሚቴውን የአገልግሎት ዘመን ለሁለተኛ ጊዜ ማራዘም ይችላል፡፡

2. ተግባርና ሃላፊነት:-

ሀ. እንዲወገዱ ለተጠየቁ የመንግሥት ንብረቶች የሚያስፈልጉ የማስወገጃ መጠይቆች፣ መረጃዎችና ሠነዶች ተሟልተው ንዲቀርቡ ያደርጋል፣ ያረጋግጣል፣

ለ. በዚህ መመሪያ በተገለጹት የማስወገጃ መመዘኛዎችና የማስወገጃ ዘዴዎች መሠረት የቀረቡ ሰነዶችን ይገመግማል፡፡

ሐ. እንዲወገዱ ጥያቄ የቀረበባቸው የመንግሥት ንብረቶች ባሉበት ቦታ በመገኘት ለውሣኔ የሚረዱ ግምገማዎችን ያደርጋል፡፡

መ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከሀ-ሐ በተገለጹት ግምገማዎች ላይ በመመሥረት የውሣኔ ሃሳብ ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊ ያቀርባል፡፡

ሠ. እንዲሸጡ ውሣኔ የተሰጠባቸውን የመንግሥት ንብረቶች የጨረታ መነሻ ዋጋ ያወጣል፣ በጨረታ ሰነድ ላይ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

ረ. የጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

ሰ. ማስታወቂያ ያወጣል፣ ጨረታ ይከፍታል፣ ያጫርታል፣ የጨረታውንም ውጤት ለንብረት ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 30. የንብረት ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ

የንብረት ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ በኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ የሚቋቋም አምስት አባላት ያሉት ኮሚቴ ሲሆን አወቃቀሩ፣ የስብሰባ ስርዓቱና የአገልግሎት ዘመኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሠ) እንደተመለከተው ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

1. የንብረት ሽያጭ ጨረታ አፈጻጸም ይህንን መመሪያ የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
2. የንብረት ሽያጭ ጨረታ ውጤት መርምሮ ያፀድቃል፡፡

## 31. ተደጋጋሚ ጨረታ የማውጣት ሂደት

1. ኤጀንሲው የሚወገዱ ንብረቶችን በጨረታ ወይም በሐራጅ ሽያጭ ከመነሻ ዋጋ ግምት ባላነሰ ዋጋ መሸጥ አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በወጣው ግምት መሠረት በቂ ተወዳዳሪ ወይም ገዢ ካልቀረበ ለሁለተኛ ዙር ለጨረታ ወይም ለሐራጅ ሽያጭ በድጋሚ መቅረብ አለባቸው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተገለፀው መሠረት በሁለተኛ ዙር መነሻ ዋጋው ለመሸጥ ተሞክሮ በቂ ተወዳዳሪ/ገዢ ካልተገኘ የግምት ዋጋውን በማሻሻል ለሶስተኛ ጊዜ የጨረታ/የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ በማውጣት በተገኘው ዋጋ ሽያጩ ይፈፀማል፡፡

## 32. ከማስወገድ ስለሚገኘው ገቢ

1. ኤጀንሲው ንብረት በሚሸጥበት ጊዜ ዋጋውን በጥሬ ገንዘብ ወይም በተረጋገጠ ቼክ ወይም በባንክ ዲፖዚት መቀበል አለበት፡፡ ያገኘውንም ገቢ ወደ ኤጀንሲው የባንክ ሂሣብ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለፀው መሠረት ሽያጩ ከተከናወነ ኤጀንሲዉ ጨረታውን ለማከናወን ያወጣውን ወጭና ከሽያጭ የተገኘውን ገቢ በመዘርዘር ሽያጩ እንደተፈጸመ ለኢንቨስትመንትና ፈንድ ስራ አመራር ዳሬክቶሬት በወቅቱ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## 33. ንብረቶችን ከመዝገብ ስለመሠረዝ

1. ከመጋዘን ወጪ የሆኑ ንብረቶች በተጠቃሚዎች እጅ ያሉ የመበላሸት፣ የመጥፋት፣ የመቃጠል ወይም በእርጅናና ሌሎች ምክንያቶች ንብረቶችን መዝገብ መሰረዝ ሲያስፈልግ የፌዴራል መንግሥት የሂሣብ አያያዝ መመሪያን በመከተል ይፈጸማል፡፡

2. ማናቸውም የኤጀንሲው ንብረት ሲሰረዝ ንብረቱ ከመዝገብ የተሰረዘበትን ምክንያትና የንብረቱ የመዝገብ ዋጋ በኤጀንሲው ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ መገለጽ አለበት፡፡

## 34. ከቀረጥ ነጻ ስለሚገቡ ዕቃዎች

ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ ስለ ቀረጡ አከፋፈል ሁኔታ የጉምሩክ አዋጅን ለማስፈፀም በሚወጡ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 35. ስለባለቤትነት ስም ዝውውር

1. ኤጀንሲው የሸጠበትን ገንዘብ ተቀብሎ የሸጣቸውን ተሽከርካሪዎች፣ መሣሪያዎችና ሌሎችም የስም ዝውውር የሚያስፈልጋቸው ንብረቶች በገዥው ስም ተመዝግቦ የባለቤትነት መታወቂያ እንዲሰጠው ስልጣን የተሰጠውን አካል በደብዳቤ በመጠየቅ ማስፈጸም ይኖርበታል፡፡

2. ኤጀንሲው በሚጽፈው ደብዳቤ ላይ የሽያጩን ቃለ ጉባኤ፣ የገዥውን ስም፣ በጨረታ የተሸጠበትን ገንዘብ ልክ፣ የተሸጠውን ንብረት መለያ ቁጥር፣ አይነትና ሞዴል፣ ተሽከርካሪዎችን የሻንሲና የሞተር ቁጥር እንዲሁም የሌሎች ንብረቶችን ሌሎች መለያዎች በመዘርዘርና የጉምሩክ ቀረጥ የተከፈለበትን ሰነድ በማያያዝ የማይከፈልበትም ከሆነ ይህንኑ በመግለጽ ማስተላለፍ አለበት፡፡

## 36. ለኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ የሚቀርብ አቤቱታ የሚታይበት ስርዓት

1. የንብረት ገዢ አቤቱታ የማቅረብ መብት

   ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ የተመለከተውን በአግባቡ አልፈጸሙም በሚል ቅር የተሰኘ ተጫራች/ገዢ ጨረታው እንደገና እንዲታይለት ወይም ሂደቱ እንዲጣራለት ለኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. አቤቱታ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች

   ሀ. ኤጀንሲው በመረጠው የንብረት ማስወገድ ዘዴ ላይ፣

   ለ. በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የሽያጭ መነሻ ዋጋ ላይ፣

   ሐ. በሚከተሉት ምክንያቶች ጨረታውን ውድቅ ለማድረግ በተሰጠ ውሳኔ

      I. በሽያጭ አካሄዱ ላይ ውጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈጸሙ ከተረጋገጠ፣

II. የኤጀንሲው ፍላጎት ለማሟሟላት ሌላ የተሻለ የማስወገጃ አማራጭ መገኘቱ በኤጀንሲው ከታመነ፣

III. የቀረበው ከፍተኛ ዋጋ ኤጀንሲው ካስቀመጠው የመሸጫ መነሻ ዋጋ ያነሰ ከሆነ፣

IV. በዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም በሽያጭ ኮሚቴ አባላት ጨረታውን ለማዛባት የመመሳጠር ተግባር መፈጸሙ ከተረጋገጠ፣

V. አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ተጫራቶች በመቅረባቸው ምክንያት በቂ ውድድር ባለመደረጉ ተስማሚ የሽያጭ ዋጋ ባለመገኘቱ፣

## 37. ለኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ የሚቀርብ አቤቱታ የሚጣራበት ስርዓት

1. ኤጀንሲው የጨረታውን ወይም የአቤቱታውን ውጤት ለተጫራቹ ከገለጸበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር ሰባት የሥራ ቀናት በፊት ሽያጩን አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር መፈጸም የለበትም፣

2. በንብረት ሽያጭ አፈጻጸም ሂደት ቅር የተሰኘ ገዢ ለአቤቱታው መሰረት የሆነውን የመጨረሻ ውሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5/አምስት/ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን በመጀመሪያ ማቅረብ ያለበት ለኤጀንሲው ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ለኤጀንሲው የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

3. አቤቱታውን ባቀረበው ንብረት ገዢ እና በኤጀንሲው መካከል ያለው ልዩነት በስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ አቤቱታ ካቀረበበት ቀን አንስቶ በ10 /አስር/ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቀረበው አቤቱታ ውሳኔውን በጽሑፍ መስጠት አለበት፡፡ በጽሑፍ የተሰጠው ውሳኔ የውሳኔውን ምንነትና የሚወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡

4. ኤጀንሲው የሰጠው የውሳኔ ግልባጭ ውሳኔው በተሰጠ በ5/አምስት/ የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ላቀረበው ንብረት ገዢ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡